የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፳፫
አዲስ አበባ– ሰኔ ፬ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 23
ADDIS ABABA–11th June, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፮/፲፱፻፺፬ ዓ·ም
ሀገር አቀፍ የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት እና የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ................................ ገጽ ፩ሺ፯፻፶፫

## CONTENTS

Proclamation No. 276/2002
National HIV/AIDS Prevention and Control Council and the HIV/AIDS Prevention and Control Office Establishment Proclamation .................... Page 1753

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፮/፲፱፻፺፬
### ሀገር አቀፍ የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት እና የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ በኢትዮጵያ በከፍተኛ ደረጃ በመስፋፋት ላይ የሚገኝ ተላላፊ በሽታ በመሆኑ፤

በሽታው በግለሰቦች ላይ ከሚፈጥረው የሕመም ስቃይና ሞት፣ በተጨማሪ በርካታና ውስብስብ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን የሚያስከትል በመሆኑ፤

ኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ቅንጅት ያለውና በሕዝብ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ የመከላከልና የቁጥጥር ዘመቻ ተደርጎበት ሥርጭቱ ካልተገታ በስተቀር ሊያስከትል የሚችለው የጤና፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ቀውስ እጅግ የሚያስፈራ በመሆኑ፤

የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ሥርጭትን ለመግታት የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተና በስፋት የሚያሳትፍ ሀገር አቀፍ አካል እንዲሁም ራሱን የቻለ መንግሥታዊ አስፈጻሚ መሥሪያ ቤት ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ሀገር አቀፍ የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት እና የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፮/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### *PROCLAMATION NO.276/2002*
### *A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE NATIONAL HIV/AIDS PREVENTION AND CONTROL COUNCIL AND THE HIV/AIDS PREVENTION AND CONTROL OFFICE*

*WHEREAS, HIV/AIDS* is a communicable disease which is spreading at an alarming rate in Ethiopia;

*WHEREAS,* in addition to the suffering and death it may cause to individuals, the disease has serious impact on the complex socio-economic development of the country;

*WHEREAS,* unless contained through a concerted multifaceted prevention and control campaign based on popular participation, *HIV/AIDS* will cause a health and socio-economic crisis that is extremely disastrous;

*WHEREAS,* to contain the spread of *HIV/AIDS,* it has become necessary to establish a national body, that involves various governmental and non-governmental organizations as well as various sectors of the society, and an autonomous government executive organ;

*NOW, THEREFORE,* in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### *PART ONE*
### *General*

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the "National HIV/AIDS Prevention and Control Council and the HIV/AIDS Prevention and Control Office Establishment Proclamation No. 276/2002".

የንዱ ዋጋ 3·40
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩· "ምክር ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ የተቋቋመው ሀገር አቀፍ የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት ነው፣

፪· "ጽሕፈት ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ የተቋቋመው የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ነው፣

፫· "ክልል" ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፵፯/፩/ በተደነገገው መሠረት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል የሆነ ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድርንና የድሬዳዋ ከተማ ምክር ቤትን ይጨምራል፣

፬· «መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት» ማለት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል ሕጋዊ አቋም ያለውና ኤች·አይ·ቪ/ኤድስ በመከላከልና በመቆጣጠር ተግባር ተሳትፎ ያለው ማኅበር፣የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም የሃይማኖት ተቋም ነው።

## ክፍል ሁለት
## ሀገር አቀፍ የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት

፫· መቋቋም

ሀገር አቀፍ የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፬· የምክር ቤቱ አባላት

ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣

፩· የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፣
፪· የፌዴራል መንግሥት ሚኒስትሮች፣
፫· የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ፣
፬· የክልል ርዕሳነ መስተዳድር፣
፭· በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ፣
፮· የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽነር፣
፯· የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽነር፣
፰· የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽነር፣
፱· የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊና የሥራ አመራር ቦርድ አባላት፣
፲· የሚከተሉት የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ኃላፊዎች፣
   ሀ) የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት፣
   ለ) የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት፣
   ሐ) የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፣
   መ) በምክር ቤቱ የሚሰየሙ ሌሎች የመገናኛ ብዙሃን ተቋሞች፣
፲፩· የሚከተሉት የሃይማኖት ተቋሞች መሪዎች፣
   ሀ) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን፣
   ለ) የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት፣
   ሐ) የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን፣
   መ) የኢትዮጵያ ወንጌላዊት መካነየሱስ ቤተክርስቲያን፣
   ሠ) የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት፣
፲፪· የክርስቲያን በጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት ዲሬክተር፣
፲፫· የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ፕሬዚዳንት፡፡



2. *Definitions*

In this Proclamation, unless the contest requires otherwise;

1) "Council" means the HIV/AIDS Prevention and Control Council established unde Article 3 of this Proclamation;
2) "Office" means the HIV/AIDS Prevention and Control Office established under Article 8 of this Proclamation;
3) "Region" means a member state of the Federal Democratic Republic of Ethiopia as provided for under Article 47/(1) of the Constitution and includes the Addis Ababa City Administration and Dire Dawa City Council;
4) "Non-governmental organization" means an association, a charitable organization, or a religious institution having a legal status allowing it to operate at a national level and which is participating in the prevention and control of HIV/AIDS.

## *PART TWO*
## *The National HIV/AIDS Prevention and Control Council*

3. *Establishment*

The National HIV/AIDS Prevention and Control is hereby established.

4. *Members of the Council*

The Council shall be presided over by the President of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and shall have the following members:

1) the Deputy Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;
2) Ministers of the Federal Government;
3) the Speaker of the House of Peoples, Representatives;
4) Heads of Regions;
5) the Head of Women's Affairs in the Office of the Prime Minister
6) the Disaster Prevention and Preparedness Commissioner;
7) the Federal Civil Service Commissioner;
8) the Science and Technology Commissioner,
9) the Head and Management Board members of the Office,
10) Heads of the following mass media organizations:
    (a) the Ethiopian Radio and Television Agency;
    (b) the Ethiopian News Agency;
    (c) the Ethiopian Press Agency;
    (d) Other mass media Organizations to be designated by the Council;
11). Leaders of the following religious institutions:
    (a) the Ethiopian Orthodox Church
    (b) the Ethiopian Islamic Affairs Supreme Council;
    (c) the Ethiopian Catholic Secretariat;
    (d) the Ethiopian Evangelical Church of Mekaneyesus;
    (e) the Evangelical Church Fellowship of Ethiopia;
12) the Director of the Christian Relief and Development Association;
13) the President of the Ethiopian Red Cross Society;

፲፬· የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያ ማኅበር ፕሬዚዳንት፣
፲፭· የኢትዮጵያ ህክምና ማኅበር ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት፣
፲፮· የኢትዮጵያ አሠራዎች ማኅበር ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት፣
፲፰· የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት፣
፲፱· የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ፕሬዚዳንት፣
፳· ከኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ዜጎች ማኅበራት መሪዎች፣
፳፩· የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪/፬/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በምክር ቤቱ የሚሰየሙ ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኃላፊዎች፣
፳፪· በምክር ቤቱ የሚሰየሙ ታዋቂ ግለሰቦች ።

፭· <u>የምክር ቤቱ ዓላማዎች</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፣

፩· ኤች·አይ·ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አግባብ ያላቸው አካላት ለችግሩ ይበልጥ ትኩረት ሰጥተው እንዲንቀሳቀሱ በማድረግና የኅብረተሰቡን ግንዛቤ እንዲ ያጎለብቱ በማበረታታት ጤናማ አመለካከትና ባህሪ የሚዳብርበትን ሁኔታ መቀየስ፣
፪· በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደረጉት ኤች·አይ·ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ጥረቶች በተናጠል ሳይሆን በተቀናጀ መልክ እንዲካሄዱና ወጣቶችና ሴቶችን ጨምሮ ለበሽታው ይበልጥ የተጋለጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ራሳቸውን ከበሽታው ለመከላከል እንዲችሉ አስፈላጊውን እርዳታና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
፫· ከኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችና በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ልጆች የጤና ፣ የሥነ ልቡናና የምክር አገልግሎትና አስፈላጊውን የማቴሪያል ድጋፍ የሚያገኙበትን እንዲሁም ሰብአዊ መብታቸው የሚከበርበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
፬· የአገሪቱ የኤድስ ፖሊሲ ከአጠቃላይ የጤና ፖሊሲው ጋር ተቀናጅቶ ተግባር ላይ የሚውልበትን መንገድ ለመቀየስና የበሽታውን ሥርጭት ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል ዕቅድና ስትራቴጂ ለመንደፍ የሚረዱ ሃሳቦችን ማመንጨትና ከዚሁ ጋር የተያያዙ የጥናትና የምርምር ተግባሮችን ማበረታታት፣
፭· በተጠናከረና በተቀናጀ መልክ ፕሮግራሞችን ለማስ ፈጸም ከአገር ውስጥና ከውጭ እርዳታ የሚሰባሰብበትን ሁኔታ ማመቻቸት።

፮· <u>የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

፩· ዓላማውን ለማስፈጸም በሚረዱ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ ሃሳብ ያመነጫል፣
፪· ከአገር ውስጥና ከውጭ እርዳታ ለማሰብሰብ ለለጋሾች ጥሪ ያቀርባል፣ ስለዕርዳታው አጠቃቀም አጠቃላይ አመራር ይሰጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣
፫· የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ፕሮግራሞችን አፈጻጸምና በዚሁ ዙሪያ የመንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ቅንጅታዊ እንቅስቃሴ ይገመግማል፣ የማሻሻያና የማጠናከሪያ ሃሳቦችን ያቀርባል፣
፬· በኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ተግባራት አመርቂ ውጤት ላስገኙ ተቋማትና ግለሰቦች ሽልማት ይሰጣል፣
፭· የራሱን ዓርማ ቅርጽና ይዘት ይወስናል፣
፮· ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሃሳቦችን የሚያመነጩ ኮሚቴዎች ያቋቁማል።

14) the President of the Ethiopian Family Guidance Association;
15) the President of the Ethiopian Medical Practitioners Association;
16) the President of the Ethiopian Labour Unions Confederation;
17) the President of the Federation of Ethiopian Employers' Associations;
18) the President of the Ethiopian Chamber of Commerce;
19) the President of the Federation of Ethiopian Teachers' Associations;
20) Leaders of associations of persons living with HIV/AIDS;
21) without prejudice to the provisions of Article 2(4) of this Proclamation, Heads of other non-governmental organizations to be designated by the Council;
22) Prominent individuals to be designated by the Council.

5. *Objectives of the Council*

The objectives of the Council due to:

1) mobilize concerned bodies to give greater attention to the problem and encourage them to enhance the society's level of awareness about HIV/AIDS and thereby promote the development of healthy attitude and behaviour,
2) to create conditions whereby nationwide prevention and control activities are carried out not through scattered efforts but in an integrated manner and vulnerable sectors of the society including youths and women are provided with the necessay support and assistance in protecting themselves against disease;
3) create conducive environment whereby people lving with HIV/AIDS and orphans obtain health, psychological, counseling services as well as the provision of necessary assistance and ensure the full protection of their rights;
4) to generate ideas for drawing an agreement of the country's HIV/AIDS Policy with the framework of the overall Health Policy and the development of future plans and strategies for monitoring and evaluating the situation on the spread of the disease; and facilitate studies and research related thereto;
5) mobilize local and external resources for implementing programs in a strengthened and integrated manner.

6. *Powers and Duties of the Council*

The Council shall have the powers and duties to:

1) deliberate on all matters that could contribute to the realization of its objectives; generate ideas and follow up their implementation;
2) extend a call on local and external donors to provide assistance; guide and oversee the utilization thereof;
3) evaluate the execution of HIV/AIDS programs and the concerted actions of governmental and non-governmental organizations; generate ideas for the improvement and enhancement of same;
4) give awards of merit to institutions and individuals who have accomplished remarkable task in HIV/AIDS prevention and control efforts;
5) determine the shape and content of its own emblem;
6) establish committees to generate ideas necessary for the realization of its objectives.

፯· የምክር ቤቱ ስብሰባዎች

፩· የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በየስድስት ወሩ ይካሄዳል ሆኖም በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፤

፪· ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡

፫· የምክር ቤቱ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡

፬· የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፤ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## ክፍል ሦስት
## የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት

፰· መቋቋም

፩· የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

፪· የጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፤

፱· ዋና መሥሪያ ቤት

የጽሕፈት ቤቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል

፲· ዓላማ

የጽሕፈት ቤቱ ዓላማ የአገሪቱን የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ፖሊሲ አፈጻጸም ማስተባበርና መምራት ይሆናል።

፲፩· ሥልጣንና ተግባር

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩· የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፤

፪· የምክር ቤቱን አስተያየት አካቶ የተዘጋጀ አገር አቀፍ የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፕሮግራም ለመንግሥት አቅርቦ ያስጸድቃል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ያስተባብራል፤

፫· ኤች·አይ·ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚንቀሳቀሱ የፌዴራልና የክልል መንግሥታዊ አካላትንና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ያስተባብራል፤ የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፬· ኅብረተሰቡ ስለኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ግንዛቤ እንዲኖረው አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎችና ዓውደ ጥናቶች ያዘጋጃል፤ እንዲዘጋጁም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

፭· ኤች·አይ·ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ ስብሰባዎች ይሳተፋል፤

፮· በአገሪቱ ያለውን የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ገፅታ መረጃዎች ያሰባስባል፤ ያጠናቅራል፤ እንዳስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸው ሁሉ ያሰራጫል፤

፯· ከተለያዩ ለጋሾች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ ይቀይሳል፤

፰· በልገሳ የተገኘው ገንዘብና ከመንግሥት የሚመደበው በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

፱· የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ውል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከሳል፡ ይከሰሳል፤

፲· ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

7. *Meetings of the Council*

1. Regular meetings of the Council shall be held every six months; provided, however, that extra-ordinary meetings may be called any time.
2) There shall be a quorum where more than hlaf of the members of the Council are present at any meeting.
3). The Council shall pass its decisions by majority vote and, in case of a tie, the Chairman shall have a casting vote.
4). Without prejudice to the provisions of this Article, the Council may adopt its rules or procedure.

## *PART THREE*
## *The HIV/AIDS Prevention and Control Office*

8. *Establishment*

1) The HIV/AIDS Prevention and Control Office is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality.
2) The Office shall be accountable to the Prime Minister.

9. *Headquarter*

The Office shall have its headquarter in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

10. *Objectives*

The objectives of the Office shall be to coordinate and direct the implementation of the country's HIV/AIDS Policy.

11. *Powers and Duties*

The Office shall have the powers and duties to:

1) serve as the secretariat of the Council;
2) submit for the approval of the Government a national HIV/AIDS program prepared on the basis of the recommendations of the Council; follow up and coordinate the implementation of same;
3) Coordinate the activities of federal and regional goverment organs and non-governmental organizations engaged in HIV/AIDS prevention and control activities and facilitate conditons for integration;
4) organize local and international meetings and workshops for enhancing the awareness of the society about HIV/AIDS and faclitate conditions for organizing same;
5) participate in national and international conferences on prevention and control of HIV/AIDS;
6) collect and compile information on the general situation of HIV/AIDS in the coutnry and disseminate same to all concerned, as deemed necessary;
7) draw a devise whereby support is obtained by creating contact with viarous donors;
8) ensure that the money secured in donation and the budget allocated by the Government is properly utilized;
9) own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;
10) perform other duties necessary for the realization of its objectives.

፲፪· የጽሕፈት ቤቱ አቋም

ጽሕፈት ቤቱ፣

፩· የሥራ አመራር ቦርድ፣

፪· በመንግሥት የሚሾም አንድ ኃላፊ እና

፫· አስፈላጊው ሠራተኞች ፤

ይኖሩታል።

፲፫· ስለቦርድ አባላት

፩· የሥራ አመራር ቦርዱ የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ፖሊሲን በማስፈጸም ረገድ ጉልህ ሚና ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የምክር ቤቱ አባላት ከሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተውጣጡ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል። ቁጥራቸውም እንዳስፈላጊነቱ ይወሰናል።

፪· የቦርዱ ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በመንግሥት ይመደባል።

፲፬· የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

የሥራ አመራር ቦርዱ፣

፩· ጽሕፈት ቤቱ የሚከታተላቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በተቀናጀ መልክ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፤

፪· ከፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ጋር ተያይዘው በሚነሱና አመራር በሚሹ ጉዳዮች ላይ እንደአግባቡ ውሳኔ ይሰጣል፤ ወይም ከአስተያየቱ ጋር ለመንግሥት ያቀርባል፤

፫· የጽሕፈት ቤቱን መዋቅርና የሰው ኃይል ፕላን መርምሮ ለመንግሥት ያቀርባል፤

፬· ለመንግሥት የሚቀርበውን የጽሕፈት ቤቱን በጀትና ሪፖርት ያጸድቃል፤

፭· በጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ በሚቀርቡለት ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል፤ ይወስናል።

፲፭· የቦርዱ ስብሰባ

፩· ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤

፪· ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፤

፫· ቦርዱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሃሳብ የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፤

፬· የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፤ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፲፮· የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

፩· የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ የጽሕፈት ቤቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ በቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ፤

ሀ) በቦርዱ ስብሰባዎች በአባልነት ይሳተፋል፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባሮች በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ) በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

12. *Organization of the Office*

The office shall have:

1) a Management Board;
2) a Head to be appointed by the Government; and
3) the necessary staff.

13. *Members of the Board*

1) Members of the Borad shall be designated by the Government from government institutions having significant role in the implementation of the HIV/AIDS policy and from non-governmental organizations which are represented in the Council; Their number shall be determined as may be necessary.
2) The Chairperson shall be designated by the Government from among members of the Board.

14. *Powers and Duties of the Board*

The Management Board shall have the powers and duties to:

1) provide guidance and spuervision to ensure the coordinated implementation of programs and projects falling under the responsibility of the Office;
2) decide on issues requiring guidance in connection with the implementation of programs and projects or submit its recommendation thereon to the government, as may be appropriate;
3) review and submit to the goverment the organizaitonal structure and manning plan of the Office;
4) approve the budget and report of the Office to be sumbitted to the Govement;
5) deliberate and decide on other matters submitted by the Head of the Office.

15 *Meetings of the Board*

1) The Board shall meet once in a month; provided however, that it may meet at any time at the request of the Chairperson.
2) There shall be a quorum where more than half of the members are present at a meeting of the Board.
3) Decisons of the Board shall be passed by majority vote and, in case of a tie, Chairperson shall have a casting vote.
4) Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may adopt its own rules of precedure.

16. *Powers and Duties of the Head of the Office*

1) The Head of the Office shall be the chief executive officer of the Office and shall, subject to the general directives of the Board, direct and administer the activities of the Office.
2) Without limiting the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Head of the Office shall:
   (a) participate in the meetings of the Board as a member;
   (b) exercise the powers and duties of the Office specified under Article 11 of this Proclamation;
   (c) employ and administer the employees of the Office in accordance with the federal civil service laws;

መ) የጽሕፈት ቤቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሥራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

ሠ) ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፣

ረ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፣

ሰ) የጽሕፈት ቤቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል።

፫· የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ለጽሕፈት ቤቱ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለጽሕፈት ቤቱ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤ ሆኖም እርሱ በማይኖርበት ጊዜ የሚወከለው ሰው ከ30 ቀናት በላይ የሚሠራ ከሆነ ውክልናው አስቀድሞ ለቦርዱ ቀርቦ መፈቀድ አለበት።

፲፯· በጀት

፩· የጽሕፈት ቤቱ መደበኛ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

፪· ጽሕፈት ቤቱ ለሚያስፈጽማቸው ፕሮጀክቶች የሚያስፈልገው በጀት ከመንግሥት፣ በለጋሽ ድርጅቶችና በኅብረተሰቡ ከሚደረግ የገንዘብ መዋጮና ከውጭ ከሚገኝ የመንግሥት ብድር የተውጣጣ ይሆናል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተመለከተው በጀት የገንዘብ መዋጮዎቹ ከተደረጉበት የብድርና የዕርዳታ ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩና በሥራ አመራር ቦርዱ በጸደቀ የጽሕፈት ቤቱ የግዥና የወጭ አፈጻጸም ሥርዓት መሠረት በጥቅም ላይ ይውላል።

፲፰· የባንክ ሂሳብ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ /፪/ የተመለከተው ገንዘብ በጽሕፈት ቤቱ ስም በባንክ ተቀማጭ ይሆናል።

፲፱· የሂሳብ መዛግብት

፩· ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፪/ ለተመለከቱት የገንዘብ ምንጮች የተለያዩ የሂሳብ መዘገቦች ይይዛል፣

፪· የጽሕፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራሉ።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳· የመተባበር ግዴታ

ጽሕፈት ቤቱ የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ ፖሊሲ አፈጻጸምን በማስተባበርና በመምራት ረገድ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

፳፩· ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።



(d) prepare and sumbit to the Management Board the Work program and budget of the Office; and implement same upon approval;

(e) effect expenditure in accordance with the approved budget and work program of the Office;

(f) represent the Office in all its dealings with third parties;

(g) prepare and sumbit to the Board the operational and financial reports of the Office.

3) The Head of the Office may delegate part of his powers and duties to the officials and other employees of the Office to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Office; provided, however, that in the case of an official who acts on behalf of the Head of the Office for more than thirty days, approval of the Board shall be required.

17. *Budget*

1) The operational budget to the Office shall be allocated by the Government.

2) The budget that the Office requires for the execution of projects shall be drawn from financial contributions by the Government, donor agencies and the community at large and from external borrowings by the Government as well.

3) The budget referred to in Sub-Article (2) of this Article shall be utilized in conformity with the credit and grant agreements under which contributions have been made and in accordance with the disbursement procedure of the Office approved by the Board of Management.

18. *Bank Accounts*

The fund referred to in Sub-Article (2) of Article 17 hereof shall be deposited in a bank account in the name of the Office.

19. *Book of Accounts*

1) The Office shall keep separate books of accounts for the funds referred to in Sub-Articles (1) and (2) of Article 17 hereof.

2) The books of accounts and financial documents of the Office shall be audited by the Auditor General or by an auditor designated by him.

## *PART FOUR*
## *Miscellaneous Provisions*

20. *Duty to Cooperate*

The concerned federal and regional government organs and non-governmental organizations shall have the duty to co-operate with the Office with a view to enabling it to effectively discharge its responsibilities with regard to coordinating and directing the implementation of the HIV/AIDS Policy.

21. *Inapplicable Laws*

No law, regulations, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have force or effect in respect of matters provided for by this Proclamation.

፳፪· <u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

የኤች·አይ·ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት በመባል የሚታወቀው አካል መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለጽሕፈት ቤቱ ተላልፈዋል።

፳፫· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፬ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፬ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



22. *Transfer of Rights and Obligations*

The rights and obligations of the organ known as the HIV/AIDS prevention and Control Secretariat are hereby transferred to the Office.

23. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 11th day of June, 2002.

Done at Addis Ababa, this 11th day of June, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE